# 2ኛ ጴጥሮስ (43)

## ጥናት አንድ 2ኛ ጴጥ 1፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- እያንዳንዳችን በክርስቶስ ኢየሱስ በሚገኘው ህይወት እያደግንና ሥር እየሰድን እንድንሄድ እግዚአብሄር የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጥቶናል፤ የእኛ ሃላፊነት ግን ለእድገታችን እንዲጠቅመን እግዚአብሄር ያዘጋጀልንን መንገዶች ማለትም ጸሎት፣ የቅዱሳን ህብረት፣ ቃሉን ማንበብና የመሳሰሉትን በሙሉ ትጋት መከታተል እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ለህይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ሃይል ሰጥቶናል… በዚህም ምክንያት በሙሉ ትጋት በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ለመጨመር ጣሩ፤›› 2ኛ ጴጥ 1፡3-5

1. 2ኛ ጴጥ 1፡1-11 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስን በምን ዓይነት ነው የሚያስተዋውቀው? ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ እምነታችን አመጣጥ ምን ይነግረናል? የእግዚአብሄርን ጸጋና ሰላም በሙላት መለማመድ የፈለገ አማኝ ማድረግ የሚገባው አንድ ነገር ምንድነው? የእግዚአብሄር ጸጋና ሰላም እንዲበዛልህ እያደረግህ ያለኸው ነገር ምን አለ?
2. በቁ3 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር ለሁለት ዋና ዋና ሁኔታዎች የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ እንደሰጠን ይነግረናል። እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? የእነዚህ ሁለት ነገሮች ለአማኝ መሰጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተረዳኸውን ተናገር። እግዚአብሄር ይህንን ሁሉ በጎነትና መልካምነትን ሲያደርግልን፤ በዚህ ሁሉ ውስጥ የእኛ ተሳትፎ ምን እንደሆነ ነው የምናነበው?
3. በቁ4 ላይ ጴጥሮስ ታላቅና ክቡር የሆነ ተስፋ በማለት የሚናገረው ስለ ምንድነው? ‹‹በእነዚህ ነገሮች አማካኝነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል›› በዚህ ክፍል ላይ ‹‹እነዚህ ነገሮች›› የተባሉት የትኞቹ ነገሮች ናቸው? በዓለም ለሚሆነው ምግባረ ብልሹነት ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው ነገር ምንድነው?
4. ትጋት ማሳየት ስለሚኖርብን ምክንያት አድርጎ ሊነግረን ሲጀምር ‹‹በዚህም ምክንያት›› በማለት ቁ5 ይጀምራል። ይህ ምክንያት ብሎ የሚናገረው ነገር ምንድነው ብለህ ነው የምትረዳው? ከዚህ ክፍል ከምናየው ነገር በመነሳት ለአማኝ ህይወት እድገት የእግዚአብሄርና የሰውየው አስተዋጽዖ ምን እንደሆነ አስረዳ።
5. ሐዋርያው ጴጥሮስ በቁ5-7 ላይ የሰፈሩት ነገሮች በህይወታችን እንዲታዩ ሲያበረታታን፤ በምን ያህል መጠን እንዲኖሩን ነው የሚፈለገው? የእነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች በአማኝ ህይወት ውስጥ መገኘት ሊያስከትሉ የሚችሏቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? ቁ2 ‹‹ኢየሱስን በማወቅ›› ቁ3 ‹‹እርሱን በማወቅ›› ቁ8 ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ›› ይላል። ኢየሱስን የማወቅ ጉዳይ በዚህ ክፍል ስለተሰጠው ሥፍራ ምን ይታይሃል?
6. ቁ9 ሲናገር በቁ5-7 ላይ የተዘረዘሩት ባህርያት የሌሉት ሰው ምን ዓይነት አማኝ እንደሆነ ያሳየናል። በዚህ ቁጥር 9 ላይ እነዚህ ባህርያት ስለሌሉት ሰዎች ጴጥሮስ የሚጠቅሳቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
7. በቁ10-11 በሚገኘው ክፍል መሰረት ሰው በእግዚአብሄር መመረጡንና መጠራቱን የሚያረጋግጥበት መንገድ ምን እንደሆነ ነው የምናየው?
8. በቁ5-7ትን መለስ ብለን ስንመለከት፤ አማኝ በእምነት ላይ መጨመር ስለሚኖርበት ባህርያት ሲናገር ‹‹በሙሉ ትጋት›› ነው የሚለው። ከዚህ አነጋገሩ የምትረዳው ምንድነው? በክርስቶስ ባለህ ህይወት እድገት ለማሳየት በጸሎት፣ ከቅዱሳን ጋራ ህብረት በማድረግና፣ ቃሉን በማጥናት ምን ያህል ትጋትን ታሳያለህ? እግዚአብሄር ለህይወትና እርሱን ለመምሰል አስፈላጊውን ሁሉ ስለሰጠን አንተ ደግሞ በትጋት ወደ እርሱ ለማደግ ተገቢውን ሁሉ አድርግ።

በወንድሙ ሃብተወልድ ተዘጋጀ (253) 653-4707 ethiowengel.com

# ጥናት ሁለት 2ኛ ጴጥ 1፡12-21

የጥናት ዓላማ፡- ከሐዋርያው ጴጥሮስ አነጋገርና ድርጊት እንደምንረዳው ምንም እንኳን አገልጋዮች መንጋውን ለማሳደግ አስፈላጊውን ትጋት ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸው ብናውቅም፤ በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ አማኝ ለራሱ መንፈሳዊ እድገት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅበት ሊያውቅ እንደሚገባው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በዚህም ምክንያት በሙሉ ትጋት በእምነታችሁ ላይ በጎነትን…እነዚህን ነገሮች ከተለየኊችሁም በኋላ ዘወትር ታስቡ ዘንድ እተጋለሁ፡፡›› 2ኛ ጴጥ 1፡5 1፡15

1. 2ኛ ጴጥ 1፡12-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ8 እና በቁ9 ላይ ‹‹እነዚህ ባህርያት›› ፤ በቁ10 ላይ ‹‹እነዚህን ብታደርጉ››፤ በቁ12 ላይ ደግሞ ሁለት ጊዜ ‹‹እነዚህ ነገሮች›› በማለት ሐዋርያው የሚናገረው ስለየትኞቹ ነገሮች ነው? ከቁ12ት አነገገር እነዚህን ነገሮች የሚያሳስበው ለምን ዓይነት ሰዎች ነው ብለህ ታምናለህ?
2. ቁ12 ‹‹ዘወትር ከማሳሰብ ቸል አልልም›› ቁ13 ‹‹እናንተን መነትነት ትክክል ሆኖ ይታየኛል›› ከሚሉት አነጋገሮቹ ጴጥሮስ ለነዚህ ነገሮች ስለሚሰጣቸው ትኩረት ምን መረዳት እንችላለን? ሰዎችን መነትነት ባብዛኛው ተቀባይነት የሌለው ድርጊት እንደሆነ የሚገባን ሲሆን፤ ለዎችን በተለይም ክርስትያኖችን መነትነት የሚገባን ጊዜ አለ ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ፡፡ አንተስ ለወገኖች ይበጃቸዋል በምትለው ነገር ምን ያህል ደጋግሞ ማሳሰብን ታደርጋለህ?
3. በቁ14 አነጋገር ስትመለከት ሐዋርያው ጴጥሮስ ለመነትነቱ ተጨማሪ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው ትላለህ? ምንም እንኳን እነዚህ ነገሮች አስፈላጊነታቸውን ቢረዳም፤ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከዚህ ምድራዊ ድንኳኑ ከተሰናበተ በኋላ እነሱን ማስተማርም ሆነ መምከር እንደማይችል ገብቶታል፡፡ በምድር እንድንሰራው የተሰጠንን የጌታን አገልግሎት አስመልክቶ ከዚህ የጴጥሮስ አነጋገር ምን መማር እንችላለን?
4. ጴጥሮስ በቁ16-18 ላይ የሚናገረው ነገር የትኛውን ልምምዱን ተመርኩዞ ነው? እነጴጥሮስ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይልና ስለመምጣቱ ለመናገር፤ የነጴጥሮስ ስለዚህ ሁኔታ የሚሰጡት ምስክርነት ከሌሎች ሰዎች ምስክርነት የሚለይባቸው ምክንያቶች ምን ምንድናቸው ብለህ ታምናለህ?
5. እግዚአብሄር አብ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላለው አመለካከት ይህ ክፍል የሚነግረንን ቢያንስ ሁለት ሃሳቦች ተናገር፡፡ በተለያዩ የወንጌል ክፍሎች ውስጥ ወልድ ለአብ ክብር ሲሰጥ እናነባለን፤ በዚህ ክፍል ማለትም በቁ16-18 ውስጥ ስናይ እግዚአብሄር አብ ለወልድ ሲሰጥ የምንመለከታቸው ሁለት ነገሮችስ ምንና ምንድናቸው?
6. በቁ19 ላይ ጴጥሮስ ‹‹እንግዲያስ ትንቢታዊው ቃል ይበልጥ ተረጋግጧል›› በማለት በተራራው ላይ በተመለከቱትና ከተለማመዱት ልምድ የተነሳ የበለጠ እርግጠኛነት እንደተገኘ አድርጎ የሚናገረው ስለየትኛው ትንቢት ነው?
7. ቁ19ኝን ስናነብ ይህንን ነብያቱ የተናገሩትን የትንቢት ቃል ጴጥሮስ እንደምን አድርጎ ነው የሚያቀርበው? ይህ የትንቢት ቃል ብርሃኑን የሚሰጠው? በአጠቃላይ ቁጥር 19 ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ፡፡
8. ቁ2021ድን ስትመለከት ስለ እግዚአብሄር ቃል እንድናውቅና እንድንረዳ ጴጥሮስ የሚፈልገው ዋነኛ ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
9. ቁ15ትን መለስ ብለን ስንመለከት ጴጥሮስ በሥጋው ከእነርሱ ከተለያቸው በኋላ እንዲያስቡ የሚፈልገው ነገር ምንድነው? ቁ5 ላይ የሚያስተምራቸው ሰዎች ትጋት እንዲያሳዩ ሲያሳስባቸው፤ በቁ15 ላይ ደግሞ በውስጣቸው ዘልቆ እንዲገባ እርሱ እንደሚተጋ እናነባለን፡፡ ከነዚህ ሃሳቦች በመነሳት አገልጋዮችና የሚገለገሉ ሰዎች ሊኖራቸው ስለሚገባ ሃላፊነት ምን እንማራለን? ራስህን እንደ አገልጋይም ሆነ እንደ ተገልጋይ ብትመለከት ለሌሎችም ሆነ ለራስህ መንፈሳዊ እድገት ትጋትን ማሳየት እንደሚጠበቅብህ ልትረዳ ያስፈልግሃል፡፡

# ጥናት ሶስት 2ኛ ጴጥ 2፡1-22

የጥናት ዓላማ፦ አንዳንድ ጊዜ በአመጽና በተንኮል የራሳቸውን ህይወት ከመምራት አልፈው ሌሎችንም የሚያስቱ ሰዎች እያበቡና እየለመለሙ የሄዱ ቢመስለንም፤ እግዚአብሄር ግን አመጸኞችን የሚቀጣበትና በእውነት እርሱን የሚያመልኩትን ደግሞ ከፈተና አድኖ ለዘለዓለም ቤታቸው የሚያበቃበት ቀን እንደቀጠረላቸው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹ጌታ በእውነት እያመለኩት የሚኖሩትን ከፈተና እንዴት እንደሚያድናቸውና ዐመጸኞችን እየቀጣ ለፍርድ ቀን እንዴት ጠብቆ እንደሚያቆያቸው ያውቃል።›› 2ኛ ጴጥ 2፡9

1. 2ኛ ጴጥ 2፡1-22 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ‹‹ሃሰተኞች ነብያት በህዝቡ መካከል እንደነበሩ›› ሲል ስለየትኞቹ ህዝቦች ነው የሚናገረው? ስለቀድሞው ዘመን ሲናገር ‹‹ሃሰተኞች ነብያት››፣ ስለእኛ ዘመን ሲናገር ደግሞ ‹‹ሃሰተኞች መምህራን›› በማለት የለየበት ምክንያት ምንድነው ብለህ ታስባለህ?
2. የሐሰተኛ መምህራኑ ስለሚያደርጓቸው ነገሮች በቁ1-3 ውስጥ ሰፍረው የምታያቸውን በመዘርዘር ተናገር። እነዚህ ሰዎች በሚያደርጓቸው ነገሮች ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን የሚጎዱበትን ቢያንስ ሁለት ነገሮች ይህ ክፍል ይነግረናል፤ እነዚህ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እንደነዚህ ዓይነት በፈጠራ ታሪክ ጎበዞች ሆነው ቅዱሳንን የሚበዘብዙ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃል ወይ?
3. በነዚሁ ቁጥሮች ማለትም በቁ1-3 ውስጥ ስንመለከት የእነዚህን የሐሰተኛ መምህራን የወደፊት እጣ እድላቸው ምን መሆኑን ነው የሚነግረን?
4. በእነዚህ በሐሰተኞች መምህራን ላይ እግዚአብሄር ሳይፈርድ እንደማይቀር ለማረጋገጥ በቁ4-9 ውስጥ ጴጥሮስ በምሳሌነት የተጠቀመባቸው ሶስት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በተለይም ደግሞ የሰዶምና የገሞራን ጥፋት ሲናገር፤ ለምንድነው እግዚአብሄር በነዚህ ከተሞች ላይ የፈረደው ይላል?
5. እግዚአብሄር ዐመጸኞችን ለፍርድ ጠብቆ እንደሚያቆያቸው ቁ 9 ላይ እናነባለን፤ በቁ10-12 ላይ ግን በተለይ ጸሐፊው ያተኮረባቸው ሰዎች ምን እንደሚመስሉና ምን ብሎ እንደሚጠራቸው ተናገር። በይሁዳ 8-9 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ በምን መንገድ ነው በዚህ በቁ10-11 የምናነበውን ሃሳብ ለመረዳት የሚጠቅመን?
6. ቁ13-18 እነዚህን ሰዎች ለመግለጽ ከተጠቀመባቸው ሃሳቦች መሃል ጥቂቶቹን ዘርዝር። ጴጥሮስ አብዛኛውን መልዕክቱን በነዚህ በሃሰት አስተማሪዎች ላይ ነው ያተኮረው። ለምን ይመስልሃል ጴጥሮስ ሌላ ብዙ ሊጽፍና ሊያስተምራቸው የሚችልበትን መድረክ በነዚህ የሃሰት አስተማሪዎች ላይ ማተኮር የወሰነው? እኛስ የሰዎችን እምነት የሚገለብጡትንና የሃሰት ትምህርትን የሚዘሩትን ማንነታቸውን ለማጋለጥ ዝግጁነት አለን ወይ?
7. በቁ18-22 ላይ ስናነብ እነዚህ ሃሰተኛ አስተማሪዎች ሌሎችን ሰዎች ለማሳትና ለማታለል የሚጠቀሙበት ዘዴ ምንድነው ይላል? እነዚህ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች የሚገቡት የተሳሳተ ተስፋ ምን የሚል ነው? የሚሰጡትን ተስፋ ስሜት የማይሰጥና ትክክለኛ ተስፋ እንዳልሆነ የሚያስረዳው ነገር ምንድነው?
8. ወደ ቁ9 ተመልሰን ስንመለከት፤ እግዚአብሄር ከፈተና የሚያድናቸውና በሌላ በኩል ደግሞ ለፍርድ ጠብቆ የሚያቆያቸው ሰዎች እነማን ናቸው? አንተስ ራስህን ከየትኞቹ ውስጥ ታያለህ? አመጸኞችም ሆኑ በእውነት ጌታን የሚያመልኩ ለሁለቱም እግዚአብሄር ዋጋቸውን የሚከፍልበት ቀን እንዳለው ልንዘነጋ አይገባንም።

# <u>ጥናት አራት 2ኛ ጴጥ 3፡1-18</u>

የጥናት ዓላማ፡- የጌታ መዘግየት ሰዎች ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ በመፈለግ የሚታገስ ስለሆነ፤ የእርሱን መምጣት የምንናፍቅ አማኞች ሁላችን ማድረግ የሚኖርብን የተሰጠንን የወንጌል ተልዕኮ በትጋት መፈጸም እንደሆነ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ደግሞ የእግዚአብሄርን ቀን እየተጠባበቃችሁ መምጫውን ልታፋጥኑ ይገባል፡፡›› 2ጴጥ 3፤12

1. 2ኛ ጴጥ 3፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2 ላይ ስንመለከት ሐዋርያው ጴጥሮስ ለነዚህ ሰዎች ከዚህ መልዕክቱ አስቀድሞ ስንት መልዕክቶችን ነው የጻፈላቸው? ጸሐፊው ለአንባቢዎቹ መልዕክቱን ሲጽፍ ሁለት ዋና ዓላማዎች እንደነበሩት በዚህ ክፍል ውስጥ ይነግረናል፤ እነዚህ ሁለት ዓላማዎቹ ምንና ምን እንደነበሩ ተናገር፡፡
2. ቁ2 ላይ ‹‹ደግሞም ቀድሞ በቅዱሳን ነብያት የተነገረውን ቃል…›› በማለት ጴጥሮስ ሲናገር እናነባለን፡፡ ለምንድነው ሐዋርያው ጴጥሮስ ‹‹‹በነብያት የተነገረውን›› ከማለት ይልቅ ‹‹በቅዱሳን ነብያት የተነገረውን›› በማለት ለቃሉ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት ያስፈለገው? ከቁ2 አነጋገር ስታይ እነዚህ አንባቢዎቹ ሙሉ የሆነውን የእግዚአብሄር ቃል እንዲያስቡና እንዲያሰላስሉ እንደፈለገ የምናውቀው ከየትኛው አነጋገሩ ነው?
3. ቁ3-7ን ስናነብ የጴጥሮስን መልዕክት የሚያነቡት ሰዎች እንዲያውቁ የፈለገው አንድ ነገር ምንድነው? በቁ4 ላይ ‹‹እመጣለሁ ያለው ታዲያ የት አለ?›› ብለው በሚናገሩት አነጋገራቸው ክርስቶስ ኢየሱስን በምን አይነት ነው የሚያቀርቡት? እንደተናገረው እንደማይመጣ ለማረጋገጥ የተጠቀሙበት ሃሳብ ምንድነው? የክህደታቸውን ዓይነት ጴጥሮስ ምን በማለት ነው በቁ5 ላይ የሚገልጠው?
4. ቁ8-9 ላይ እግዚአብሄር ከሰው የሚለይበት አድርጎ ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ የሚያስረዳው ሃሳብ ምንድነው? ጴጥሮስ ‹‹በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ አመት፣ ሺህ አመትም እንደ አንድ ቀን መሆኑን…›› በማለት ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? ጴጥሮስ ለመዘግየቱ ምን ትርጉም ነው የሚሰጠው? ከመዘግየቱ የሚገኘው ውጤትስ ምን ሊሆን ይችላል? አንተስ የጌታን መዘግየት በዚህ መልኩ አይተኸው ታውቃለህ ወይ?
5. ቁ10-11 ጸሐፊው የጌታን መምጣት ከምን ጋራ ነው እያነጻጸረ የሚናገረው? ጌታ ሲገለጥ ስለሚሆኑ ሶስት ትላልቅ ነገሮች ተናግሯል፤ እነዚህ ሶስት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ጴጥሮስ ከዚህ ሁሉ ነገር እኛ አማኞች ልንቀስም ስለሚገባን ትምህርት ምንድነው የሚመክረን?
6. ቁ12-13 ዘባቾቹ ስለጌታ መምጣት የተስፋ ቃል ሲያላግጡ፤ በነዚህ ቁጥሮች መሰረት አማኞች ከእነርሱ የተለዩ ሆነው የሚገኙት በምን መንገድ ነው? ቁ12 ‹‹እየተጠባበቃችሁ›› ቁ13 ‹‹እንጠባበቃለን›› ቁ14 ‹‹የምትጠባበቁ›› የሚሉት ቃላት ክርስትያኖች የጌታን ምጻት አስመልክቶ ህይወታቸውን በምን ዓይነት እንዲኖሩ ነው የሚያበረታታው? አንተስ ህይወትህን የምትኖረው በዚህ መንገድ ነው ወይ?
7. ቁ14-18ትን ስናነብ ጴጥሮስ ስለጳውሎስ የተናገራቸው ነገሮች ምንድናቸው? የጳውሎስን መልዕክቶችንም ሆነ ሌሎችን ቅዱሳን መጻህፍት የሚያጣምሙትን ሰዎች ጴጥሮስ ምን እያለ ነው የሚጠራቸው? በቁ17 ላይ ጴጥሮስ ከዚህ አንጻር አንባቢዎቹን ምን እንዲያደርጉ ነው የሚመክራቸው?
8. በቀ12 ላይ ስንመለከት አማኞች የጌታን መምጫ እንዲያፋጥኑ ይመክራቸዋል፡፡ የጌታን መምጣት አማኝ በምን መንገድ ማፋጠን ይችላል ብለህ ታምናለህ? የጌታን ምጻት ለማስቸኮል እያደረግህ ያለኸው ምን ነገር አለ? ጌታ የሚዘገየው ወይም የሚታገሰው ሰዎች ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ ወዶ ስለሆነ፤ ሰዎችን ለንስሃ የሚያበቃውን የወንጌሉን መልዕክት ለሰዎች ሁሉ በማድረስ መምጣቱን ማስቸኮል ትችላለህ፡፡